## የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ግጭት፡ ፓልቶክ ደርሶ መልስ

**ከጌታቸው ኃይሌ**

የካቲት 1 ቀን 2001 (02/08/09) በሁለት ፖልቶክ ውይይት ላይ እንድሳተፍ ተጋብዤ የጠቀሙኝ ሰዓቶች አሳለፍኩ። የመጀመሪያው ***በግል ሕይወቴ ከደረሰውና ካጋጠመኝ አንዳፍታ ላውጋችሁ*** በሚል ርእስ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፳፻ ዓ.ም. ስለአሳተምኩት መጽሐፍ ሲሆን፥ ሁለተኛው ሰሞኑን በኢትዮጵያ ውስጥ በሙስሊሞቹና በክርስቲያኖቹ ኅብረተሰብ መካከል ስለተነሣው አለመግባባት አስተያየቴን ለማሰማትና ለሌሎችም ከዚያው ጉዳይ ጋር ተያይዘው ለሚነሡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ነበር። የመጀመሪያውን ግብዣ ሳልግደረደር፥ እንዲያውም ማንም ሊገምተው በሚችል ምክንያት፥ በደስታ ተቀበልኩት፤ ስለሁለተኛው ግብዣ ግን ለምን ከኔ የተሻለ ሰው አትፈልጉም በማለት አመንትቼ ነበር። "እነሱ ተጋብዘው መጥተው ነበር" የሚል መልስ ሳገኝ ግብዣውን በስጋትና በምስጋና ተቀበልኩ። ይቺን አጭር ማስታወሻ የምጽፈው በስጋት ስለተቀበልኩት ስለሁለተኛው ግብዣ ነው።

በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ገዢዎች የሚጠቀሙባቸው ሰውን የሚያቀራርቡና የሚያራርቁ ክሥተቶች አሉ። ሕዝብ ያልተቀበላቸው ገዢዎች ሰው የሚያጣሉትን ነገሮች ይኮተኩቷቸዋል፤ ዘዴው አዲስ ስላይደለ፥ ማብራሪያ አያስፈልገውም፤ ሰውን አጣልቶ የዳኝነት ለመብላት ነው። አገር አስፋፊዎችና ሕዝብ ገምቢዎች ደግሞ ሰው በሚያፋቅሩት ነገሮች ላይ ያተኩራሉ፤ "አንድ ነን እኮ" ሲሉ ይሰማሉ። ግን ሕዝብ በፈቃዱና በፍላጎቱ ያላቋቋመው አስተዳደር ሁሉ፥ አገር አስፋፊም ቢሆን እንኳ፥ በሁለቱም ዘዴዎች የሚጠቀምበት ጊዜ ይኖራል። በተለየ በከፋፍለህ ግዛው ፖለቲካ የተጠቀሙ የቅርብ ተንኮለኛ ገዢዎች የኢጣሊያ ፋሽስቶችና የአሁኖቹ የትግራይ ፋሺስቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለቱ ሃይማኖቶች የሚገፋፉቸው ካለ፥ የመቀራረቢያና የመራራቂያ እንዲያውም የግጪት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ክሥተቶች ናቸው።

ሃይማኖት የግጪት ምክንያት ሊሆን እንደሚችልና መሆኑንም ከታሪክ እያነበብንና አሁንም ከዜና ዘጋቢዎች እየሰማን፥ "ምንም የለም" ከማለት የሚሻለውና የሚገባን የሚያዋጣውን መፍትሔ መፈለግ ነው። የዛሬውን ግጭት የጫሩት የሚመጣውን ምርጫ የፈሩ ፋሺስቶቱ የትግሬ ገዢዎቻችን መሆናቸውን አንርሳ። አገርን በእሳት ለማጋየት አንድ ሕፃን ልጅ አንዲት ክብሪት ቢጭር እሳቱ ይቀጣጠላል። ማጥፋቱ ግን አንድ የእሳት አደጋ ሠራዊት ሊያሸንፍ ይችላል። ስለዚህ ነው ሳይቀጣጠል በቅጠል የሚባለው። የሁለቱም ወገን የሃይማኖት መሪዎችና ሽማግሌዎች ተነጋገረው ክብሪት ጫሪውን ካላሳፈሩት የፈለገውን መስጠት ይሆናል።

በሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ስላለው ግንኙነት አስተያየት ስሰጥ የአንዱ ሃይማኖት ተከታይ በመሆኔ የማዳላት መልስ የምሰጥ የመሰላቸው መኖሩን በማየቴ ትንሽ ቅር ቢለኝም፥ ውይይቱ የተካሄደው ሰላምን በሚፈልጉ ኢትዮጵያውን መካከል በኢትዮጵያዊ ጨዋነት በመሆኑ በደስታና በተስፋ ደርሼ ተመልሻለሁ። በውይይቱም ጊዜ ሆነ ወይም በዚህ ጽሑፍ ሚዛናዊ ለመሆን እንጂ፥ የየትኛው ሃይማኖት ተከታይ መሆኔን የሚያሳዩ ምልክቶችን ለመደበቅ አልተጨነቅሁም። ደግሞስ ከማን ነው የምደብቀው?

ከታሪክ እንደተገነዘብኩት፥ ጉዳዩን የምናየው ከሁለት አቅጣጫ መሆን አለበት፤ በመንግሥትና በሕዝብ ደረጃ። በሕዝብ ደረጃ ሲታይ ከወያኔዎች አገዛዝ በፊት በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ሊተች የሚገባው ነፍስ ያለበት ግጪት ትዝ አይለኝም። ይህን ምስክርነት የምሰጠው እኔ ብቻ ሳልሆን በድር ጭምር ነው። የበድር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ማህበር ለትግሬ ወያኔ መሪ ለመለስ ዜናዊ ሚያዝያ 1999 (ዓ.ም.) የጻፈው ደብዳቤ እንዲህ የሚል የምስክር ቃል ይዟል፥ "የመንግስትን ታሪክ ከህዝብ ታሪክ ለይተን ማየት ያለብን በመሆኑ

*በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል የከፋ ግንኙነት ነበር ብለን አናምንም።" ኢትዮጵያን የሰላም ሀገር ለማድረግ ተስፋ የሚሰጥ ምስክርነት ነው።*

*በመንግሥት ደረጃ ግን ችግር ነበረ፤ መንሥኤው ይለወጥ እንጂ አሁንም አለ። ከአማውቃቸው ሙስሊሞች ውስጥ የኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥት እንደሚጨቁናቸው ምርር አድርገው የሚናገሩ ነበሩ። በውይይቱ ላይም አንዳንድ ሙስሊሞች ከአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት* (1307-1336) *ጀምረው ታሪክ እየጠቀሱ ሙስሊሞች በመንግሥት ደረጃ እንዴት ይጨቆኑ እንደነበረ አስረዱ። "ኢትዮጵያ የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች አገር ሆና ሳለ ክርስቲያኖቹ የክርስቲያን ደሴት ይሏታል" እያሉ አማረሩ። መቸም ቢሆን ታሪክ የሚጠቀሰው ከሁለት ምክንያቶች ላንዱ ነው--ወይ ለመርታት ወይ መፍትሔ ለመፈለግ። ለመርታት ሲሆን መረቻውን እየደበቁ መርቻው ብቻ ይጠቀሳል፤ መፍትሔ ለመፈለግ ግን በሽታን ለሐኪም የመንገር ያህል ሁሉም ፍርጥርጥ ብሎ ይወጣል።*

*በምንም ምክንያት ይሁን፥ ፓልቶኩ ላይ የተጠቀሰው ታሪክ በተሟላ መልኩ አይደለም። ጥቅሱ እውነትነት ቢኖረውም ጐደሎ ነው፤ ለማሟላት ያህል፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ክርስቲያኖቹ ጥርቃሞ ጎሳዎችን ሰባስበው የፈጠሯት ሀገር ናት፤ መንግሥቱም፥ ክርስቲያኖቹ ስላቋቋሙት የነሱ መንግሥት ነበረ። ታሪኩ በአንስታይ ጾታ "መንግሥት መሲሐዊት" ይላታል። ክርስቲያኖች ያቋቋሙት መንግሥት "የክርስቲያኖች መንግሥት" ቢሆንና ቢባል ስሕተቱ ከምኑ ላይ ነው? እስቲ እስራኤላውያንንና የዓረብ ሀገር ባለሥልጣኖችን ስለራሳቸው መንግሥታት እንጠይቃቸውና ምን እንደሚሉ እንስማቸው?*

*"ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" ማለትም በሀገሪቱ ውስጥ ሌላ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች አይኖርባትም ማለት ሳይሆን፥ በእነሱ ማህል የክርስቲያን መንግሥት* (*"መንግሥት መሲሐዊት"*) *ያለባት ሀገር ናት ማለት ነው። በአንድ በኩል "መንግሥቱ የክርስቲያኖች እንጂ እኛ ሙስሊሞች ድርሻ የለንም" ብሎ፥ ያንን አዳምጠን ሳንጨርስ ወዲያው "የክርስቲያን ደሴት አትበሏት" ብሎ መቆጣት የአስተሳሰብ ቅራኔ ነው። እንዲያውም በዛሬው ዘመን ቢሆን ብዙ ሙስሊሞችና የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ባሉበት ሀገር "መንግሥቱ የክርስቲያኖች ብቻ ነው" ማለት ጨቋኝነትን በይፋ መናገር ነው።*

*ኢትዮጵያ ውስጥ የክርስቲያን መንግሥት ማቋቋም ራሱን የቻል የማያስወቅስ ታሪክና ሊያስወቅስ የሚችል ችግር አለው። በማያስወቅስ ታሪኳ ልጀምርና፥ ኢትዮጵያ በተፈጠረችበት አካባቢ ያሉ መንግሥታት ሁሉ የተፈጠሩት እንደ ኢትዮጵያ ሃይማኖትን መሠረት አድርገው ነው። በሃይማኖት ባህል ላይ ያልተቋቋመ መንግሥት የለም። የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችም እንደሌሎቹ አገር ሕዝቦች መንግሥት በማቋቋማቸው ኢትዮጵያን ጥንታዊትና ባለባህል አሰኝተዋታል፤ በበኩላችን ጥንታውያንና የባህል ጌቶች ስላደረጉን እንኮራባቸዋለን።*

*በማህል ቤት ሌላ ሃይማኖት ገባ፤ እስላም ማለቴ ነው። እስላምን መጤ ሃይማኖት የሚሉ ካሉ፥ ክርስትና ቤት ሠርቶ ኮርቶ በመቶ በሚቈጠሩ ዓመታት በተቀመጠበት አገር መጥቶ ስለገባበት ነው። የቅድሚያ ጉዳይ ነው እንጂ፥ ሃይማኖቶች ኢትዮጵያን ጨምሮ ዓለምን የወረሩት ከአንድ ቦታ እየመጡ ነው። እስላምን መጤ የሚያሰኘው ሌላም ምክንያት አለው--እንደ ኮሎኒያሊስቶች የባህል ወራሪነት ጠባይ ይታይበታል። የሱዳንን ጥቍር ሕዝብ "ዓረቦች ነን" እንዲሉ እንዳሳሰባቸው እናስታውስ። ክርስትናን ግን አባቶቻችን ኢትዮጵያ ያስገቡት ሃይማኖቱን ከባህሉ አልላቀው እንጂ፥ ከነባህሉ አይደለም። ማለት፥ አባቶቻችን እምነቱን የተቀበሉት በራሳቸው ፊደልና በራሳቸው ቋንቋ ነው። በዚያ ላይ በራሳቸው ሥነ ጽሑፍ ኢትዮጵያዊነት መልክ እየሰጡት በየእኛነት አዳብረውታል።*

*ሌላ ምሳሌ ላምጣ፤ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ታላላቆቹን የጥንቶቹን የሃይማኖት አባቶች ለማስታወስ ያህል አንዳንድ ጊዜ ለልጆቻው "ጴጥሮስ"፥ "ጳውሎስ"፥ ወዘተ የሚል ስም ይሰጡ እንደሆን ነው እንጂ የክርስቲያኑ ሁሉ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ አይደለም። ለምሳሌ ጌታቸው*

የሚል ስም ያላቸው ክርስቲያኖች እንዳሉ አውቃለሁ:: በዚሁ አንጻር ሙስሊሞቹ እስልምናን እንዴት እንደተቀበሉት ስናይ ሃይማኖቱን መጤ የሚያሰኝ መጤ ባህል ሲያመጣብን እናገኘዋለን:: ኢትዮጵያ አገራችን የቋንቋ ሀብታም ሆና ሳለ÷ ሃይማኖቱ የሚጠናው በዓረቢኛ ነው:: የተከታዮቹ ስም ዓረቢኛ እንጂ ኢትዮጵኛ አይደለም:: “ዐብደላ” ማለት “ገብረ እግዚአብሔር” ማለት ነው፣ “ሐሰን” ማለት “አማረ” ማለት ነው፣ “ጀሚላ” ማለት “ቆንጂት” ማለት ነው፣ “ሐቢባ“ ማለት ውድነሽ” ማለት ነው፣ “ሙሐመድ” ማለት “ገለታ” ማለት ነው÷ “ዓሊ” ማለት “በላይነህ” ማለት ነው፣ “ሰዒድ” ማለት “ደስታ”÷ “ፍሥሐ” ማለት ነው:: “አላህ” ማለት “እግዚአብሔር” ማለት ነው:: አባቶቻችን “ቢስሚላሂ አርራሕማን አርራሒም” የሚለውን ተከትለው ሲጸልዩ “በስመ እግዚአብሔር መሐሪ ወመስተሣህል” ብለው ተርጉመው ነው:: ፈላሻዎች ራሳቸውን ቤተ እስራኤል ቢሉም በሃይማኖታቸው ሳቢያ ዕብራይስ አላመጡብንም:: ቋንቋቸው ኢትዮጵያዊ÷ ስሞቻቸው ኢትዮጵያዊ ነው::

ሃይማኖቱን አልብሶ የመጣው ባህል አለያየን፣ አንድ ሰው ስሜ ሐሰን ነው ሲለኝ ሃይማኖቱን ጭምር የነገረኝ ይመስለኛል:: የመካከለኛው ምሥራቅ ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ሳይቀር የሚማሩት በብሔራዊው ቋንቋ (በዓረቢኛ) እንጂ በራሳቸው በቅብጡ በሱርስት አይደለም:: የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ግን በባህል ረገድ “የዓረብ ጠረን” አለባቸው:: ለዓረብ ሊግ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮ የከፈቱ ሰዎች በሀገሪቱ ውስጥ ዓረቦች አሉ ብለው ሳይሆን÷ እንደ ሱዳኖቹ ዓረቦች ሊሆኑ የሚችሉ ሙስሊሞች አሉ ብለው በመገመት ነው::

ወደታሪክ እንመለስና÷ በክርስቲያን መንግሥት እስላም ገብቶ ተከታዮች ሲያበዛ ነገሥታቱ አገዛዛቸውን በመሰላቸው መንገድ ማስተካከል ነበረባቸው:: ያደረጉትም እንዲህ ነበር፣ አብዛኛው ሕዝብ የእስልምና ተከታይ በሆነበት አገር ሁሉ ነገሥታቱ የበላይነቱን ለራሳቸው ይዘው የውስጥ አስተዳደራቸውን ሙሉ በሙሉ ለቀቁላቸው:: ስለዚህ በራሳቸው ኢማም ይገዙ ጀመር:: ይኽ ዓይነት አገዛዝ ሙስሊሞቹን ዜጎች ሊያጠግባቸው ይገባ ነበር ወይስ አልነበረም? እስቲ በእነሱ ዘመን ሆነን ትክክለኛ ፍርድ እንፍረድ፣ ይህ ዓይነት አገዛዝ አያጠግብም የሚል ካለ÷ አማራጩ ምን መሆን ነበረበት? በዚያ ዘመን እስልምና የነገሠበትን ሀገር ይገዙ የነበሩ ባለ ሥልጣኖች በጥጋቸው ለሚኖሩ ክርስቲያን ዜጎቻቸው ይፈቅዱላቸው የነበረው መብት ምን ነበር? ብርቱካንን ከብርቱካን ጋር ማስተያየት ይገባል ብዬ ነው::

እስልምና በነገሠበት ሀገር ያሉ ክርስቲያኖች አቅመ ቢሶች ስለሆኑ÷ ብዙም አይጠይቁም ብዙም አይሰጣቸውም ነበር:: እኛ ዘንድ ግን ቀይ ባሕር ዳርቻ የነሱ መስፈሪያ ስለነበረ÷ በዓረብ ሀገር የሚመረትና ወደዚያ የሚመጣም የሌላ አገር የእንዱስትሪ እቃ÷ በተለየም የጦር መሣሪያ÷ በቀላል መንገድ ስለሚያገኙ ነገሥታቱ በመጠኑላቸው መብት ሊወሰኑ አልፈለጉም:: ሌላ ምን ይጨመርልን ይሉ ነበር? መልሱን አንድ ሙስሊም ጠያቂ በጠቀሰው በአፄ ዓምደ ጽዮን ታሪክ ውስጥ እናገኘዋለን::

> ዓምደ ጽዮን የሚባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ትዕቢተኛውና ዲክቴተሩ የከሐዲዎቹ ንጉሥ ራሱን ከፍ አድርጎ በፈጣሪው ላይ እንደ ተመካው እንደዲያብሎስ መክዳቱን ሰማ፣ (ዲያብሎስ÷) “እንደ ልዑል (እግዚአብሔር) እሆናለሁ” እንዳለው÷ ሰብረዲን የሚባለው የከሐዲዎች ንጉሥም ራሱን ከፍ አድርጎ በጌታው በዓምደ ጽዮን ላይ ትምክሕተኛ ሆኖ÷ “የመላይቱ ኢትዮጵያ ምድር ንጉሥ እሆናለሁ፣ ክርስቲያኖችንም በ(ሃይማኖቴ) ሕግ (አስገብቼ) እገዛቸዋለሁ፣ ቤተ ክርስቲያኖቹን አወድማቸዋለሁ” አለ:: በዚህ ቃሉ መሠረት÷ ተነሥቶ ዘመተ፣ ከክርስቲያኖች ምድር ደርሶ ቤተ (ክርስቲያን) አቃጠለ፣ ክርስቲያኖቹን ገደላቸው፣ የተረፉትን ወንዱንም ሴቱንም ማርኮ ከሃይማኖቱ አስገባቸው:: ከዚያ በኋላ÷ “በኢትዮጵያ ብሔሮች ላይ የጽዮን ንጉሥ (ዓምደ ጽዮን) ገዢዎች እንደሚሾም እሾምባቸዋለሁ” አለና÷ ገዢዎች (መኳንንት) እና መሳፍንት ሾመ፣ በዳሞት ላይ አንድ መስፍን÷ በወረብ ላይ አንድ መስፍን÷ . . .

ታሪኩ እንዲህ እያለ ብሔሮቹንና የሾሙባቸውን ሰዎች ማዕርግ መዘርዘሩን ይቀጥላል፣

> ወጊ÷ አላማሌ÷ ፈጠጋር÷ እንደገብጠን÷ ሽሜ÷ ሙገር÷ ግራርያ÷ ጽላልሽ÷ ከተታ÷ ወግዳ÷ ሰርማት÷ ክልአት÷ ጽሕጋ÷ ተጕለት÷ ምድረ ዝጋ÷ መንዝ÷ አምሓራ÷ ሰገራት÷ አንጎት÷ ቅዳ÷ ማእከለ ተዋዛት÷ ማእከለ ባሕር÷ እንደርታ÷ በጌምድር÷ ጕዣም፡፡ መድረስ ከማይችልበት (ብሔር) ሳይቀር በምድረ ኢትዮጵያ ሳይሾምበት የቀረ ምድር አልነበረም፡፡ ግን እግር ራስ÷ ምድርም ሰማይ÷ ሎሌ ጌታ አይሆኑም፤ ያ ከሐዲ የተናዳፊ እባብ (አፍኦት) እና የመርዛም እባብ (ቃግስማ) ልጅ የሌሎች÷ የሰይጣን ዝርያ ግን የዳዊትን ዙፋን ተመኝቶ÷ "በጽዮን እኔ እነግሣለሁ" አለ፡፡ እንደ አባቱ እንደ ዲያብሎስ ትዕቢት በልቡ ገብቶ÷ "አብያተ ክርስቲያኑን የሙስሊሞች መስጊድ አደርጋቸዋለሁ፤ ክርስቲያኑን ንጉሥም ከነሕዝቡ ወደ ሃይማኖቴ ሕግ አስገባውና ከገዢዎቹ አንዱ አደርገዋለሁ፤ አልሰልምም ካለ÷ የግመል ጠባቂ እንዲያደርጉት ወርጅሕ ለሚባሉ ከብት እረኞች እዳርገዋለሁ፡፡ የንጉሡን እቴጌ ንግሥት ዣን መንገሣን ወፍጮ አስፈጫታለሁ፡፡ መዲናውን መርዓዴን መዲናዬ አደርጋታሉ፡፡

ንጉሡ ይኸን ሰምቶ በቁጣ ጦርነቱን ከማወጁ በፊት የተባለው እውነት እንደሆነ ለማረጋገጥ ፈልጎ÷ መጀመሪያ ዐመፀ ወደተባለው ወደ አዳሉ ንጉሥ ወደ ሰብረዲን መልክተኛ ይልካል፤ ከአመጡለት መልስ ቍርጡን ያውቀዋል፡፡ ታሪኩ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤

> ንጉሡ (ዓምደ ጽዮን) የከሐዲውን ንጉሥ ብልግና ሲሰማ ተቆጣ፤ ሰውነቱ በቁጣ ተንቀጠቀጠ፡፡ እንዲህ ብሎም ላከበት፤ "ይኸ ስላንተ የምሰማው ነገር እውነት ነው ወይስ አይደለም? የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን አቃጠልክን? ክርስቲያኖችን ገደልክን? የተረፉትንም ማርከህ እንደ አባትህ እንደ ዲያብሎስ ሕግ እንጂ እንደክርስቲያን ሕግ ወደ አልሆነው ወደ (እስላም) ሕግህ አስገባሃቸውን? ከአሁን በፊት ወንድምህ ሐቀዲን ትዕይንታይ የሚባል አንድ ትንሽ ሎሌ በወሰደ ጊዜ ያደረግሁትን እኔን አታውቀኝምን?" . . .
>
> (ሰብረዲን) ለንጉሡ እንዲህ ሲል ላከበት፤ "(እንግዲን ወዲህ ግብር ለመገበር) መጥቼ ከፊትህ አላደገድግም፡፡ ወደኔ የምትመጣ ከሆነም አልፈራም፤ ምክንያቱም÷ በሰይፍ÷ በሾተል÷ በፈረስ÷ በቀስት÷ በጋሻ÷ በጦር÷ በድምቡስ--ማለት÷ በብረት ዘንግ--በዕንጨት ጦር የሚዋጋ÷ ከሠራዊትህ የሚበልጥ ሠራዊት አለኝ፡፡ ወደኔ ለመምጣት ከፈለግህ በሰፊው ጎዳና ና፤ አለዚያ እኔ መጥቼ እገጥምሃለሁ፡፡

ባጭሩ የግጭቱ ምክንያት ኢትዮጵያን ማን የበላይ ሆኖ ይግዛት የሚለው አስተሳሰብ ነው፡፡ ተገንጥሎ ነፃ የመውጣት ነገር እንኳን የለበትም፡፡ ሀብቱ ያለው ከደጋው አገር ስለሆነ ፍላጎታቸው እንደወያኔዎቹ "እኛ እንቦጥቡጠው" ነው እንጂ÷ እንደሞኞቹ እንደሻዕቢያዎቹ "ከባሕር ዳር እንደ ብቅል ተሰጥተን ሰማይ ሰማይ ስናይ እንኑር" አልነበረም፡፡ አፄ ዓምደ ጽዮንም አቅም እስካለው ድረስ ከአባቶቹ የወረሰውንና እሱም ያስፋፋውን መንግሥት ለማንም አይለቅም፡፡ ዘምቶ መታቸው፡፡ ሕዝባዊ መንግሥት እስካልተቋቋመ ድረስ ምክንያቱና ግጭቱ አሁንም ይቀጥላል፡፡

ጥቅሱን ልብ ብለነው ከሆነ÷ አፄ ዓምደ ጽዮንና ኢማም ሐቀዲንም ቀደም ብለው ተጋጭተው ነበር፡፡ ከሌላ ምንጭ እንደምናውቀው÷ ቀጥሎ ቀዳማዊ አፄ ቴዎድሮስ÷ አፄ ዘርአ ያዕቆብ÷ አፄ ናኦድ ከኢማሞቹ ጋር ተዋግተዋል፡፡ በሰፊው የሚታወቀው ግን የኢማም አሕመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ (የግራኝ መሐመድ) እና የአፄ ልብነ ድንግል ግጭት ነው፡፡ የግራኝ ዐመፅ ታሪክ ሲነሣ÷ "እንርሳውና ወደፊት እንይ እንጂ÷ ኢማሙ ያወጀው ጂሀድ ነበር" ስል አንድ ሰው ተነሥቶ÷ "ጂሀድ ማለት ትግል ማለት ነው፤ በኢማሙ ጦርነት ጊዜ የተቃጠሉት ቤተ ክርስቲያኖች ዓሥራአንድ ብቻ ናቸው፤ የእስልምና ሃይማኖት ሰው መግደል ይከለክላል" አለን፡፡

መቸም ወደኋላ የሚታየው ያለፈው ስሕተት እንዳይደገም ለማድረግ እንጂ÷ ለበቀል አይደለም፤ ለበቀል ከሆነ ሁሉም ቢላዋውን ይስልና መተላለቁ ይቀጥላል፡፡ ጃፓንና አሜሪካ÷ ጀርመንና የቀረው አውሮፓ አብረው ሲሠሩና ዓለማቸውን ሲቀጩ÷ እኛንም ሲመጸውቱ÷ እኛ ከሰብአ ትካትነታችን (primitiveness) አንላቀቅም ካልን÷ የኔ ምክር ነቢዩ "እሳትና ውሐ አቅርቤልሃለሁ

እጅህን ከሚጠቅምህ ላይ አሳርፈው" ያለው ነው:: ከአለፈው ለመላቀቅ የምንችለው ለመርታት እየተከራከርን ሳይሆን የሆነውን ተቀብለን ታሪክ ያመጣብንን ስሕተት ለማረምና ለመቀበል ስንዘጋጅ ነው:: ምንም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያንነቴ ቢሰማኝ፥ ክርስቲያን ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼና እኅቶቼ የክርስቲያን መንግሥት ጥገኞች ሆነው ይኑሩ ልል አልችልም:: በዚያው አንጻር ሙስሊም የሆነ ሰው "ተራው የኛ ነው" ቢለኝ አልቀበልም፤ ከተቃዋሚው ጋር እሰለፋለሁ::

"ጂሀድ ማለት ትግል ማለት ነው" ማለት የደረሰውን ጉዳት ማቃለል ይሆናል፤ የሚያዋጣው የሆነውን አምኖ ወደፊት ማየቱ ነው:: ትግሉ ልጆች ከሜዳ ላይ ወጥተው "ና እንታገል፤ የሚወድቀውና የሚጥለው ይለይ" የሚሉት ዓይነት አይደለም:: " በምንም ምክንያት ወደኋላ ሳናፈገፍግ በአንድነት በእሮምታ እንዝመትበትና ድራሹን እናጥፋው" የሚል የጭካኔ ጥሪ ነው:: እርግጥ ሃይማኖቱ ነፍስ መግደል ይከለክላል፤ ግን ተከታዮቹ አንገት ቈርጠው "ነፍሱ እየተቅለበለበች ገሃነም ገባች" እያሉ ራሳቸው የጻፉትን አንብበናል::

በዚያ ጦርነት ኢትዮጵያ የወደመባት ቅርስ መጠን የለውም፤ ኢትዮጵያ ከዚያ ጥፋት እስካሁን አላንሰራራችም:: "የተቃጠሉት ወይም የወደሙት ቤተ ክርስቲያኖች ዓሥራአንድ ብቻ ናቸው" ማለትም ወደሰላም የሚመራ ሳይሆን የሚያስቆጣ ይሆናል:: ኢየሩሳሌም ያለው አልአቅሳ መስጊድ ቢቃጠልና አንድ ሰው መጥቶ "የተቃጠለው አንድ መስጊድ ብቻ ነው" ሲል ብሰማ እኔን ሙስሊም ያልሆንኩትን እንኳ ሳይቀር ያስቆጣኛል:: ደብረ ሊባኖስ፥ አክሱም ጽዮን፥ ደብረ ዳሞ፥ ደብረ ሐይቅ፥ ደብረ ቢዘን፥ መካነ ሥላሴ፥ ደብረ ሣሕል፥ ምሥሐለ ማርያም፥ አትሮንሰ ማርያም፥ ክብርቶ፥ የጣና ሐይቅ ገዳማት፥ የላሊበላ አድባራት በክርስቲያኖቹ ዘንድ እንደ አልአቅሳ መስጊድ ናቸው:: የኢማሙ ሙጃሂዲን (ታጋዮች) ደብረ ሊባኖስ ሲደርሱ መነኮሳቱ፥ "የፈለጋችሁን ውሰዱ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ግን እናታችን ናትና እባካችሁ ማሩልን" አሏቸው:: ሙጃሂዲኑ ልመናውን ተቀብለውና ተስማምተው ንብረቱን ከወሰዱ በኋላ ዞር ብለው ቤተ ክርስቲያኗን አቃጠሏት:: ከመነኮሳቱ፥ ብዙዎቹ "ከእናታችን ተለይተን አንቀርም" በማለት እየዘለሉ ከእሳት ገቡ:: ላሊበላን የከብት በረት አድርገውት ነበር:: ከክርቲያኖቹ ወታደሮች አንዱ ተሽሎክሉኮ ገብቶ አንዱን የሙጃሂዲንን መሪ በሾተል የወጋው ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሴት ጋር ተኝቶ አግኝቶት ነው:: የኢማሙ ዓረቦችና ከነሱ በፊት ኢትዮጵያን የጎበኙ ፖርቱጋሎች የመካነ ሥላሴን ውበት ሲያደንቁ ይኸን የመሰለ ሕንፃ የትም አላየንም ብለዋል:: ይህን ሁሉ ታሪክ የጻፈው አንድ ደብተራ ብቻ ሳይሆን ፉቱሕ አልሐበሻን የጻፈው ዓረብ ፈቂህ በሚል ስም የሚታወቀው የኢማሙ ታሪክ ጸሐፊ ጭምር ነው::

አንዲት ጠያቂ ጽላተ ሙሴ ኢትዮጵያ መምጣቷን ተርካ "ሀገሪቱ የእግዚአብሔር ሀገር ብትባል ጥፋቱ ወይም ስሕተቱ ከምን ላይ ነው?" ብላ ጠየቀች:: እግዚአብሔር የሚመለክበት ሀገር ሁሉ የእግዚአብሔር ሀገር ነው:: ቅዱስ ዳዊትም "ለእግዚአብሔር ምድር በምልኣ" (መሬት በመላዋ የእግዚአብሔር ነች) ብሏል:: ይኸንን "አልቦ እግዚአብሔር" ከሚሉ ኢአማንያን (Atheists) በቀር ማንም አይክድም:: ውዝግብ የሚነሣው "ኢትዮጵያና መንግሥቷ የፈጣሪዎቿ የኦርቶዶክሶቹ ሆና ትኑር፤ የኢትዮጵያዊነት መሠረቱ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሀገር ናት ማለት የእግዚአብሔር ወልድ (የመሲሑ የኢየሱስ ክርስቶስ) ሀገር ናት ማለት ነው" ሲባል ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቃልሎ እግዚአብሔርን በሌላ ሃይማኖት ቢያመልከው ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሀገር መሆኗ ቀረ ማለት ይቻላል?

ጽላቱ ከአይሁድ ሃይማኖት የተወሰደ መሆኑን ለጊዜው ብንረሳውም፥ ያለንበት ዘመን ብንወደውም ባንወደውም ሃይማኖትና መንግሥት በዓዋጅ የተፋቱበት ዘመን ነው:: የፍቺውን ሥርዓት ከፈጸሙት የፖለቲካ ካህናት አንዱ፥ "አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት ግን የግል ነው" ያሉት አፄ ኃይለ ሥላሴ ናቸው:: ይኸን ዓዋጅ ከልብ መቀበል ለጥቂቶቻችን ቀላል አይደለም:: "እሱ ሙስሊም ነው፤ እሷ ኮተሊክ ናት፤ እነሱ ፕሮቴስታንቶች ናቸው፤ የአባቶቻችንን ባህል ሳያከብሩ እንዴት ኢትዮጵያውያን ሊባሉ ይቻላል?" የምንል አንጠፋም:: ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ሀገር ነች ማለትን መስማት ለአንዳንድ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች ከባድ ይሆንባቸዋል ማለት ነው::

የያዙትን መልቀቅ ቀላል አይደለም፤ ይመርራል:: ግን ታሪክ የማይፈልጉትን ነገር እንድንቀበል ያስገድዳል:: እስጥምቡል ያለቺው ታላቋ አግያ ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን ተወስዳለች፤ ንጥቂያውን ግሪኮች በግድ ተቀብለውታል:: አሜሪካኖች ሚስተር ኦባማን በመምረጥ ግዳታውን በውዴታ ስላለፉት፥ ያለፉበት ሰላማዊው መንገዳቸው ምሳሌ እንደሚሆነን ተስፋ አለኝ:: ለምሳሌ፥ አንድ ጠዋት ጋዜጣ ስንገልጥ፥ “ኢትዮጵያ አዲስ መንግሥት አቋቋመች፤ ሼኽ አሕመድ ሑሴይን ፕሬዚዴንት፥ ሼኽ ኢድሪስ ዑመር ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኑ” የሚል ዜና ብናገኝ፥ “ምነው ይኸን ቀን ሳላይ በወሰድከኝ” ብለው የሚያዝኑ ሰዎች እንደሚኖሩ እገምታለሁ:: አዲሱ መንግሥት የተቋቋመው በዐመፅ መንግሥት በመገልበጥ ከሆነ፥ ሥጣኑን የያዙት ጳጳሶችም ቢሆኑ አዝናለሁ:: በሕዝብ ምርጫ ከሆነ ግን፥ “ሕዝብ ካለ እግዜር አለ፤ የእግዜር ስም ይባረክ” ብዬ ለሚቀጥለው ምርጫ እዘጋጃለሁ:: የምዘጋጀው ሼኾቹን ከሥልጣን ለማውረድ እንዳይመስላችሁ፤ ኢትዮጵያን ካገለገሉ መልሶ ለመምረጥ፥ ከበደሉ ለማባረር ነው:: የምንመርጠው የፖለቲካ መሪዎች እንጂ የሃይማኖት መሪዎች አይደለም:: በሃይማኖቴ አይገቡብኝም፤ ለሙስሊሞቹም አያዳሉም::

ኦርቶዶክሳውያን የፍቺውን ዓዋጅ ከልብ እንዳይቀበሉ የሚያደርጓቸው፥ አንዳንድ ምክንያቶች አሉ፤ የሚያሰጋቸው ሌላ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች መንግሥቱን መጋራታቸው ሳይሆን ሁሉም (ሙስሊሞቹም ሆኑ ሌሎቹ ክርስቲያኖች) እረኛ አልባውን የኦርቶዶክስ በግ ስለሚያጋብሱና ወገናቸውን ስለሚቀንሱባቸው ነው:: ለዚህም የውጪ ኀይል አለበት ይባላል:: ዘመቻው እርግጥ በሕገ ወጥ ወይም ሃይማኖት በማይፈቅደው መንገድ ኦርቶዶክሶቹን ለማጥፋት ከሆነ አልሞት ባይ ተጋዳይ የሚባለው ይደርሳል:: ግን አንድ ምእመን የአባቶቹ ሃይማኖት ሳይስማማው ቀርቶ ወደሌላ ከሄደ የሚሄደው ኢትዮጵያዊነቱ ተጠብቆለት በሰላም ይሸኛል::

ከሚያስጓቸው ምክንያቶች ሌለው፥ ሙስሊሞቹ ዛሬም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያኖችን ያቃጥላሉ፤ ካህናቱን ይገድላሉ:: ጃራ የተባለ ሙስሊምና ጀሌዎቹ “እድሜ ዕድሉን ለሰጡኝ ለትግሬ ወያኔዎች” እያሉ ጨርጨር ውስጥ ባለው ደብረ አሰቦ ገዳም ውስጥ የሚኖሩትን መነኮሳት በቢላዋ እንዳረዷቸው አንብበና:: ደብረ አስቦ የተመሠረተችው የዛሬ ሰባት መቶ ዓመት ግድም ነው:: በአሁኑ ዘመን ኦርቶዶክሶቹ ስንት መስጊድ አቃጠሉ? ይኸ ሁሉ መቆም አለበት:: ሌላውን ማሰብም እንኳን ባንችል፥ ከሁለቱም በኩል በሚሊዮን የሚቈጠሩ አማንያንን ማጥፋት እንደማይቻል እናስብ:: እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ::

ከንጉሡ ዓዋጅ የምረዳው አንድ ኢትዮጵያዊ አንድ የጋራ እና አንድ የግል እምነት ሊኖረው እንደሚገባ ነው:: የጋራው እምነት “ኢትዮጵያዊነት” ሲሆን የግሉ እምነት እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን የሚያመልክበት ወይም የሚክድበት መርሐ ነው:: ይኸን መርሐ ተከትለን ወደሚያደርሰን ቦታ መገሥገሥ አለብን:: ይኸንን ከማድረጋችን በፊት ግን ብሔራዊ ውገናችንን ኢትዮጵያዊነት ላይ እንድናደርግ የሕሊና መሐላ ማድረስ ይኖርብናል:: የምንለያየው ወደቤተ ጸሎት ስንሄድ ብቻ ነው:: ኢትዮጵያዊውን ሁሉ ወገኔ ነው ካልን ሕሊናና ሕግ ተከትሎ የሚገነባው ቤተ ጸሎት (ቤተ ክርስቲያንም ሆነ መስጊድ) ሊያሳስበን አይገባም:: የክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች እየሰለሙ የሙስሊሞቹን ቍጥር ሲያበዙት ክርስቲያኖች ካዘኑ፥ ማዘን የሚገባቸው ከክርስቶስ መድኃኒትነት በመራቃቸው ለእነሱ ነው እንጂ ወገን በማጣት ምክንያት መሆን የለበትም:: ጉዳዩ ካሳሰበ ለሃይማኖት መሪዎች ኀላፊነታቸውን ማስታወስ ይቻላል:: ሃይማኖት መለወጥ ወገን የማጣት ስሜት ካመጣ ግን ኢትዮጵያዊውን ከልብ አለመወገን ይሆናል:: ለማንኛውም፥ የወደፊቱን የሚያውቅ የለም እንጂ፥ በአሁኑ ሰዓት ዓዋጁና ዲሞክራሲ ኦርቶዶክሶችንም ሆነ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮችን የሚጠቅም እንጂ የሚያሰጋ ነገር የለበትም::

በአንድ ማስጠንቀቂያ ልደምድም፤ የማይተማመኑ ባልንጀራዎች በየወንዙ ይማማላሉ የሚባለው እንዳይደርስ ሁለቱም ወገኖች መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል:: ወገንተኝነት የጋራ ነው፤ አንዱ ወገኔ ሲል ሌላው አዎን እያለ ወገንነቱን ማዘናጊያ እንዳያደርገው ራሱን ይምከር:: ሀገር የጋራ የሆነችውን ያህል የሌላው ጠላትም የጋራ ነው፤ የአንዱ ኅብረተሰብ ጠላት የሌላው ኅብረተሰብ ወዳጅ ሊሆን አይችልም:: ወዳጅነት የሚጠነክረውና ሰላም የሚሰፍነው እምነት ከሚያሳጣ ሥራ ሲቆጠቡ ነው::